# የመኢአድ አባላት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደ ወህኒ መውረዳቸው ተገለጠ

በሰሜን ጎንደር ዞን በጭልጋ ወረዳ በጨንድባ ንዑስ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የነበሩ ዘጠኝ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባላት ከግንቦት ወር 2000 ዓ.ም አንሥቶ ለወራት በወረዳው ዋና ከተማ በአይከል ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ሲማቅቁ ቆይተው ባሁኑ ወቅት ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ወደ ወህኒ ቤት መውረዳቸው ተገለጠ።

በፖሊስ ጣቢያ ታስረው በነበሩበት ወቅት የደረሰባቸውን በደል ለበላይ አካል አመልክተው አንዳችም ውሣኔ ሳያገኙ የቀሩት እነዚህ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባላት “1. ዋኘው ታደሰ 2. መኳንንት ስንሻው 3. አለሀኝ መኳንንት 4. ከፈለ ታደገ 5. ደምስ የኋላ 6. ከላጅ ጀግኔ 7. ተፈራ ዓለሙ 8. ሠጠኝ ታደገና 9. እንዳለ ታደገ የተባሉ መሆናቸውንም ምንጮች አክለው ገልፀዋል።

አባላቱ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባልያዙ የፖሊስ አባላት ከየመኖሪያ ቤታቸው ተለቅመው የታሠሩ ሲሆን በግልፅ ጭብጥ የተደራጀ የክስ ቻርጅ ያልደረሳቸው መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል።

ባሁኑ ወቅት የአባላቱ ቤተሰቦች በከፍተኛ ችግር ላይ የወደቁ ሲሆን ልጆቻቸውም ትምህርታቸውን ተረጋግተው ለመከታተል እንዳልቻሉ ታውቋል።

# ሁለት የመኢአድ አባላት ቤታቸውን ተቀምተው ቤተሰቦቻቸው መበተናቸው ተገለጠ

አቶ ገነት አበሻ በመተከል ዞን በፖዌ ልዩ ወረዳ በመንደር 4. ውስጥ ነዋሪና አቶ ባትሪ ዱኔሮ በልዩ ወረዳው በቀጣና 1. በመንደር 5. ይኖሩ የነበሩ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባላት ለዓመታት የኖሩበትን የግል መኖሪያ ቤታቸውን በአገዛዙ ሹማምንት ተቀምተው ለወራት ሲንከራተቱ ቆይተው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ቤተሰቦቻቸው መበተናቸውን ምንጮች አመለከቱ።



EthioLion.com

እንደ ምንጮቹ አገላለፅ ባሁኑ ወቅት የአባላቱ ቤተሰቦች ተበትነው በከፍተኛ ችግር ላይ የሚገኙ ሲሆን ለአካለ መጠን ያደረሱ ልጆቻቸውም በአካባቢያቸው በሚገኙ ክፍት የሥራ ቦታዎች ተቀጥረው እንዳይሠሩ ማዕቀብ እንደተደረገባቸው ምንጮች አክለው አስረድተዋል።

የአካባቢው የሥርዓተ አገዛዙ ሹማምንት በሚቶቹ የመኢአድ አባላት ቤተሰቦች ላይ የደረሰባቸውን በደል በማስመልከት ሰብዓዊ እርዳታ እንዲደረግላቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ "ቅንጅት ሲነግሥ ይበላሉ። ቅንጅት ያብላቸው" በማለት የስላቅ መልስ መስጠታቸውንም ምንጮች ገልፀዋል።

የሚቶቹ አባላት መኖሪያ ቤቶች ለሥርዓቱ ታማኞች መስጠታቸውንም ከአካባቢው የዓይን ምስክሮች ለማረጋገጥ ተችሏል።

## በሣውላ የመኢአድ ጉባዔን ለማሰናከል የተደረገው ሙከራ ከሸፈ

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን በሣውላ ከተማ የልዩ ዞኑን ዓመታዊ መደበኛ የመኢአድ ጉባዔ ለማሰናከል በአገዛዙ ሹማምንት የተደረገው ሙከራ በአባላቱ ቁርጠኝነት መስከረም 11 ቀን 2001ዓ.ም ከሸፈ።

በዕለቱ አቶ ከሣሁን ካሤ በሣውላ ከተማ የዮጫ ክፍለ ከተማ ሰብሣቢ ካይሻ ከለቻ የተባለ ፖሊስና ሁለት የአካባቢ ታጣቂዎችን አስከትለው ወደ ጉባዔተኞች ዘንድ በመሄድ ጉባዔው ሕገ ወጥ መሆኑን በመናገር ለማስፈራራት ሞክረዋል።

ሆኖም ጉባዔተኞቹ መኢአድ ራሱ ሕገ ወጥነትን የሚዋጋ ሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲ መሆኑን በማረጋገጥ ማስፈራሪያውን ውድቅ አድርገዋል።

ጉባዔው በዕለቱ የቀድሞ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ስሙን ወደ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መለወጡን በሙሉ ድምፅ ተቀብሏል።

በዚህ ጉባዔ ላይ ከጎፋ ልዩ ዞን 12 ወረዳዎች የተወከሉ 120 ጉባዔተኞች ተሳትፈዋል።

## በደባርቅ ሁለት የመኢአድ አባላት መታሠራቸው ተሰማ

በሰሜን ጎንደር ዞን በደባቅር ወረዳ ውስጥ ሁለት የመኢአድ አባላት ከመስከረም 14 ቀን 2001 ዓ.ም አንስቶ በእሥር ላይ እንደሚገኙ ተሰማ።

ቄስ መሐበ ታደሰ እንዲሁም ዲያቆን ይርጋ ታከለ የተባሉ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባላት ተይዘው የታሠሩት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በፖሊስ አስገደጅነት ሲሆን የተሠሩበትም ምክንያት ያልተገለፀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ባሁኑ ወቅት የደባርቅ ወረዳ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ኮሚቴ አባላት በየዕለቱ በገዥው ፓርቲ ታጣቂዎች የማስፈራራትና የማዋከብ ሁኔታ እየተፈፀመባቸው መሆኑ ተውቋል።

## ዜጎች መሬታቸውን መቀማታቸው ተሰማ

በመተከል ዞን በፓዊ ልዩ ወረዳ ውስጥ ንፁሐን ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ብቻ የእርሻ መሬታቸውን መቀማታቸው ሰሞኑን ተሰማ።

በዚህም መሠረት አድማሱ ቦሩ በመንደር 5 የቀጣና 2፤ ጌታሁን አመኑ በመንደር 5 የአልሙ ከተማ፤ ታገለ እምቢያለ የመንደር 4፤ ሰይድ መሐመድ የመንደር 7፤ መስከ ታደገ የመንደር 5 ነዋሪዎች የእርሻ መሬታቸውን ተቀምተው ባሁኑ ወቅት ከነቤተሰቦቻቸው በከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀው እንደሚገኙ ታውቋል።

በተመሣሣይ ሁኔታ ቢልልኝ አረጋ፤ ጌትነት መከሰ፤ ሰፊነ መኳንንት፤ ግርማ ታአምራት፤ ይልቃል ዓለሙ፤ ሀብታሙ ማሩ፤ ታአምሩ ይማም፤ መሐመድ ቢካል ሰይድ መሐመድ የተባሉ የመንደር 4 ነዋሪዎች መሬታቸውን ተቀምተው ባሁኑ ወቅት ለችግር መዳረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል።

እንዲሁም ሼህ መሐመድ ዘዋገ የመንደር 7፤ ጌታው ይታፈሩ በመንደር 7 የቀጣና 1፤ ካሣዬ ዘነበ በመንደር 7 የቀጣና 1፤ አጋጨው አምታታው በመንደር 17 የቀጣና 1፤ ደህንነት ሙጩ በመንደር 16 የቀጣና 1ና ጥሩዬ መሠለ በመንደር 24 የቀጣና 2 ነዋሪዎች የእርሻ መሬታቸውን በአገዛዙ አካላት ተቀምተዋል።

EthioLion.Com